ግንቦት ፯ ቀን ፪ሺህ ፱ ዓ.ም፡

# ይድረስ ለጀርመን ድምፅ ራዲዎ ዐማርኛው አገልግሎት

<u>ቦን</u> / ጀርመን

ከሁሉ በተቀዳሚ እጅግ በጣም የከበረ ሰላምታችን ለሁላችሁም ይድረሳችሁ።
ግንቦት ፯ ቀን ፪ህ ፱ ዓ.ም << አነጋጋሪው የኦሮሚያ ልዩ ጥቅምና አዲስ አበባ>> በተሰኘ ርእስ የቀረበውን ውይይት ሰምተንነዋል። በአዜብ ታደሰና ልደት አበበ ተዘጋጅቶ የቀረበው እጅግ በጣም ጥሩ እንደነበረ እየገለጽን፤ በዚሁ አጋጣሚም ሁለቱ ባለሙያዎች ላድረጉትና ለሚያደርጉት የላቀ ችሎታ ያለን አድናቆት ከምስጋና ጋራ እናቀርባለን።

በመጀመሪያ ደረጃ በርእሰ ጉዳዩ ላይ ለመወያየት ከተጋበዙት አራት ግለሰቦች መካከል የተከበሩ ጠበቃ ተማም አባቡልጉ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ሆኑ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬ ያለበት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ቀውስ የአናሳ ኅሣ ወኪልና ነፃ አውጭ ግንባር ነኝ ባዩ የወያኔ ትግሬ ሕወሓትና ተለጣፊዎቹ ለሩብ ምዕተ ዓመት በላይ የሚያራምዱት ኢዴሞክራሲያዊ፣ ሕግየለሽ፣ ኢሰባዊ የባንቱስታን አፓርታይድ የጎሳና የዘር ፖለቲካ ፍጹም ፈላጭ ቆራጭ ሥርዓት ውጤት መሆኑን በጥልቀት ተንትነዋል። እኝኹ ዕውቅ የሕግ ባለሙያና ለሰብአዊ መብት ተከራካሪ ያቀረቡትም ዘልቂ መፍትሔ ሃሳብ ትክክለኛ ነው።
አዎ! በአዲስ አበባባ ይሁን በሌሎች ከተሞች በ1967 ዓ.ም ያለአግባብ የተወረሱት ቤቶች፣ የከተማ ቦታ፣ የንግድና የማከፋፍያ የልማትና ማምረቻ ተቋማት፣ ለባለንብረቶች በአግባቡ መመለስ ይኖርባቸዋል። እንዲሁም በወራሪው የወያኔ ትግሬ ሕወሓት ዘመን በአዲስ አበባ፤ ሌሎች ከተሞችና የባንቱስታን የጎሣ ክልሎች በሊዝ ሽፋን ያለ ተገቢ ካሳና ያለ ሕግ በገፍ የተፈናቀሉ ነዋሪዎች ይዞታና ንብረት ሲመለስላቸው ብቻ ነው የከተማዎች ልማትና እድገት፣ ሰላምና መረጋጋት የሚሰፍነው። በተረፈ የወያኔ ትግሬ ሕወሓት የጎሳና የዘር ፖለቲካ ልክ እንደ ደርግ ከሥር መሠረቱ ሲደመሰስ ብቻ ነው የአዲስ አበባ ነዋሪዎችና በዙሪያዋ ያሉት ገበሬዎች፣ የሸዋ፣ የጋምቤላ፣ የኮንሶ፣ የወልቃይት ጠገዴ ጠለምት፣ የአፋር ወዘተረፈ ነዋሪ ሕዝብ ነፃነትና መብት የሚረጋገጠው።

እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለበት ዐቢይ ጉዳይ በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚኖሩ ገበሬዎችን ከሕጋዊ ይዞታቸው ያለአግባብ የተፈናቀሉት በወያኔ ትግሬ መጤ ሠፋሪዎችና ግብረ አበር ተላላኪ በሆኑት የኦሮሞ ኦሕዴድ ተብዬ ካድሬዎች እንደሆነ በግልጽ መታወቅ አለበት። በተጨማሪም ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች ወያኔ ትግሬ ዘወትር የሚሾምላቸው ከንቲባዎች ከኦሕዴድ ታማኝ ሆዳም ካድሬዎች መሃል ተመልምሎ እንጂ የአዲስ አበባ ተወላጅና ነዋሪ ለከንቲባነት እንዲይመረጥ፤ አዲስ አበባ ከተማ የወያኔ መፈንጭያና ልዩ ጥቅም ማጋበሻ እንድትሆን በጥንቃቄ ታስቦ ነው ሕገ መንግሥት ተብዬው ያለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ተሳትፎና ይሁንታ የተዘጋጀው።
የአዲስ አበባ ሕዝብ ራስን በራሱ በዴሞክራሲያዊ ነፃ ምርጭያ የማስተዳደረ መብትና ነፃነቱን የሚቀዳጀው ወራሪው ወያኔ ትግሬ ሲቀበር ብቻ ነው። እስከዚያው ግን ለክቡር አቶ ተማም አባቡልጉ ረጅም እድሜና ጤና ይስጥልን።

ከተቃዋሚ ፓርቲ ተብዬዎች ወገን አንዱ የሆኑት አቶ ሙላቱ ገመቹ የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ ምክትል ሊቀ መንበር ለቀረበላቸው ጥያቄ "ፊንፊኔ ከተማ ልክ በአሮሚያ ክልል ውስጥ እንዳሉት ሌሎች ከተሞች ለምሳሌ አዳማ፣ አሰላ፣ ነቀምት፣ ቢሸፍቱ ወዘተረፈ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ መሆን ሲገባት ወያኔ ያለአግባብ በፌደራል መንግሥት ሥር በማድረጉ ነው ችግር የተፈጠረው" ሲሉ ተደምጠዋል።
ታዲያ! ይህ ሃሳባቸው የአዲስ አበባን እስከ ስምንት ሚሊዎን የሚጠጋ ነዋሪ ሕዝብን የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትና ነፃነት፣ በዴሞክራሲያዊ ነፃ ምርጭ አስተዳድሪዎችን መርጦ የመሾምና መሻር ሂደት የሚፀረር መሆኑን ስለምን ዘነጉት? ማንም ግለስብ ይሁን ወይም ቡድን ነፃነት የሚኖረው የሌላውን ግለስብ ነፃነት ወይም የቡድን ነፃነት እስከ አልነካ ድረስ ብቻ ነው።

የአዲስ አበባ ነዋሪ ከመቶ ሰማኒያው በላይ የኦሮሞ ኅሣ አለመሆኑ፣ በአብዛኛው የዐማራና የጉራጌ ተወላጅ መሆኑ በግልጽ እየታወቀ የኦሮሞ ብሔረተኝነትን በግዳጅ ለመጭያን የሚደረገው ፍጹም ከንቱ ምኞት የጠባብ ኅሠኝነት አባዜ ካልሆነ በቀር ምን ይባላል? እዚህ ላይ አቶ ሙላቱ ገመቹና ብጤዎቻቸው በግልጽ ሊነገራቸው የሚገባ ትልቅ ጉዳይ አለ። የናዝሬት ከተማ ነዋሪ ከ75 በመቶ በላይ ዐማራ ሲሆን ዐማራው በኦሕዴድ ካድሬዎች መብትየለሽ ሁለተኛ ዜጋ መደርጉ ስለለምን ይሸፈጣሉ?
በአጠቃላይ በኦሮሚያ ክልል ተብዬው ውስጥ የሚኖሩት በብዙ ሚሊዎን የሚቆጠሩት ዐማሮች በአገራቸው በምድራቸው ለዘወትር የጎሣስ ማጽዳትና የዘር ማጥፋት ሰለባ መሆናቸውን ዓለም ያውቀዋል።

የናዝሬት ከተማን የመሠረተውና በዚያም የሚኖረውን ዐማራ ሕዝብ በራሱ ፊደልና ቋንቋ ባማርኛ እንዳይጠቀም በወያኔ ካድሬዎች ተከልክሎ በቁቢ ላቲን ፊደል ማመልከቻ ጻፍ፣ በትምህርት ቤት ልጆችህ በቁቢ ፊደል ይማሩ ተብሎ በግዳጅ ጥቁር ፈረንጅ እንዲሆን ስለ ተዘመተበትና ግፉ ስለበዛ በአመጽ መነሳቱ ከቶ አይቀርም። በናዝሬት ከተማ ብዙሃኑ ዐማራ ግብር ከመክፈል በስተቀር በአገሩ በየረር አውራጃ ከፖለቲካውና ከኢኮኖሚው መድረክ ከተገለለ ከሩብ ምዕተ ዓመት በላይ ሆነው። እረ! ምን በናዝሬት ብቻ በድሬዳዋ፣ በሐረር፣ በደብረ ዘይት፣ በጅጅጋ፣ በአሰላ፣ በጅማ፣ ወዘተረፈ ከተሞችና ገጠር ቀበሌዎች ውስጥ የሚኖሩት ዐማሮችና ጉራጌዎች ኢትዮጵያዊ የዜግነት መብታቸውን ተገፉዋል። አብሶም በሀረሬ ክልል ተብዬው ለሚደረገው ፀረ ዐማራ የዘረኝነት ፖለቲካ የሚሰጠው የተቃውሞ አጸፉ ከግምት በላይ ይሆናል።
የኦሮሚያ ልዩ ጥቅም ተብሎ የሚለፈፈው ማወናበጃ ለኦሮሞ ጎሣዎች ጥቅም ሳይሆን ለወያኔ ትግሬና ለኦሕዴድ ቅልብ ተላላኪዎችና ዘመድ አዝማድ ልዩ ጥቅም ማጋበሻ ነው። ከዚህም ሌላ ለወያኔ ትግሬ ፋሽስት ባንቱስታን የጎሣ ፖለቲካ የኢትዮጵያን ሕዝብ ልክ እንደ ወራሪው ጣሊያን በቋንቋና ሃይማኖት ሸንሽኖ ርስ በርስ በማጋጨትና ከፋፍሎ በመግዛት ሥልጣን ላይ ለመቆየት፤ የባሕር ማዶና አካባቢው የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶችን ጥቅምና ፍላጎት በታማኝ ቅጥረኛነት ለማገልገል ታስቦና ታቅዶ የሚደረግ ሴራ ነው።
የኦሮሚያ ልዩ ጥቅም ማስገኛው ረቂቅ አዋጅ ተብዬውና አባሪው መግልጭያ የከፋፋይዎች፤ ገንጣይ አስገንጣይ የነወያኔ ሕወሓት፣ የሻዕቢያና ኦነግ ፕሮፓጋንዳ አራማጆችና በባንቱስታን የፈጠራው ኦሮሚያ ክልል ተብዬው ግዛት የነፃ አሮሚያ መንግሥትን በኢትዮጵያ ምድር ላይ ለመመሥረት የሚቃዡት ትርኪ ምርኪ ነው። ዓለም ከመፈጠሩ አስቀድሞ ፊንፊኔ የፈጠራው ኦሮሚያ ክልል ልዩ ንብረት እንደነበረች ተደርጎ ተናፍሷል፣ ይናፈሳል። ሻዕቢያ የውሽት ታሪክ ደጋግሞ በማናፈስ ኤርትራን ማስገንጠል እንደቻለው ሁሉ የኦሮሞ ብሔረተኞችና ቡድኖችም እንደነ ኦነግና ብጤዎቹ በፈጠራ ወሬ የኦሮሚያን ነፃ ሪፑብሊክ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ለመመሥርረት ስለ ቋመጡ ነው ፊንፊኔ የሚባል ከተማቸው በሸዋው አጤ ምኒልክ ቅኝ ተገዥ ሆነብን አያሉ በሬው ላም ወለድ ወሬ የሚነዙት። ማንም ማወቅ ያለብት ሐቅ አዲስ አበባ ከሁሉ በተቀዳሚ የሸዋ ሀገርና መንግሥት ዋና ከተማ፣ ቀጥሎም የመላው ኢትዮጵያና የአፍሪቃ አሕጉር መዲና ናት። በእቴጌ ጣይቱ ብጡል ብርሃን ዘኢትዮጵያ የተቆረቆረችውም በጥንት ሸዋ እንደግብጣን (መናገሻ አውራጃ) ልዩ ስሙ <u>እንዶጥና</u> ተብሎ በሚጠራው በምሥራቅ የረር ተራራ፣ በደቡብ ዝቋላ ተራራ፣ በስተምዕራብ መናገሻና ወጨጭያ ተራሮች በስተሰሜን እንጦጦ ተራራ መካክል ባለው ስፍራ ከዘመነ ዛጉዌ ሥርዎ መንግሥት ወዲህ ከ13ኛው እስክ 16ኛው መጀመሪያ አጋማሽ ድረስ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ አጤ መንግሥት መናገሻ በነረበት ነው። የዚሁ አካባቢ ነባር ሕዝብም ክርስቲያን ዐማራ፣ የሰባት ቤት ጉራጌ፣ ጋፋት፣ ዳሞት፣ ዟይና፣ ከምባታ ነገዶች ነበሩ እንጂ የወረሞ ቱላማ ጎሣዎች አልነበሩም።
በታሪክ ሰንድ ጋላ በመባል በመላው ዓለም የሚታወቁት፣ ነገር ግን ወታደራዊ ደርግ ኦሮሞ ተብለው እንዲጠሩ በአዋጅ ያስገደደላቸው መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።
የነገደ ጋላ ልዩ ልዩ ጎሣዎች በኢትዮጵያ በተለይም በሸዋ ምድር በሉባ የደፈጣ ውጊያ ስልታቸው ከጥንት ባሌ ወዲያ ቦረና ኬኒያ ጠረፍ አገራቸው በመነሳት በተከታታይ ወረራ መጥተው በቋሚ ነዋሪነት የሰፈሩት ከ17ኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ወዲህ ነው። ለጋላ ወረራ አመቺ ሁኔታን የፈጠረው የግራኝ አሕመድ የ14 ዓመታት ጅሃዳው ወረራና እልቂት ለኢትዮጵያ አጤ ማዕከላዊ የክርስቲያን መንግሥት መዳከምና ይልቁንም ከመሐል አገር መናገሻ ስፍራው ከሸዋ ወደ ሰሜን ምዕራብ ተዛውሮ በጎንደር ላይ ቋሚ መዲናውን እንዲያደርግ አስገድዶታል።

አጤ ሠርፀ ድንግል በከፍተኛ ደረጃ የጋላ ወራሪዎችን በያለበት እስከ ባሌና ሐረርጌ ድረስ ቢዋጉም እንኳ የጋላ ቱላማና ሜጭያ ጎሣዎች የአዋሽን ወንዝ ተሻግረው በደቡብና ምዕራብ ሸዋን አልፈው እስከ ዳሞት በዛንሞ፣ ምድረ ጋፋት ያለውን በጣም ለምና ሰፋፊ በሆነው የግጦሽ መሬት ከምድረ ጉራጌ ግቤ ወንዝ እስከ አባይ ወንዝ ዳርቻ ድረስ በሚገኘው ሰፌ መሬት በቋሚ ነዋሪነት ስፍረዋል። በሌላ በኩልም የወሉና ከረዩ ጎሣዎች ቤተ ዐማራንና አንጎትን ወረው እስከ ትግሬ ድረስ ተስፋፍተው መስፈራቸውን የኢትዮጵያና የአውሮፓ የዘመኑ የዓይን ምሥክሮች በስፋት መዝግበውታል።

የሸዋ አካባቢ መንግሥት የተመረተው ስለ ሁለት ነገሮች ነው። በመጀመሪያ ከአጤ ሠርፀ ድንግል ዘመነ መንግሥት ወዲህ በሸዋ አውራጃዎች በደቡብ ከጉራጌ ከዟይና ከምባታ እስከ ሰሜን መንዝና ግሼ ድረስ በያለብት ቀንደኛ ባላባቶች ተነስተው ለየራሳቸው አገር ይዘውና ተከፋፍለው በርስት ወሰንና ድንበር እየተጣሉ ከመዋጋታቸው በስተቀር አንድም የበላይ ገዥ ጸሐፊ ላም ያጤው ተሿሚና አስገባሪ አልነበረም።
በሁለተኛ ደረጃም ከፍ ብሎ እንደተገለጸው በጋላ ጎሣዎች ማለትም በቱላማና ሜጭያ፣ በከረዩ፣ በወሎ፣ በኢቱ፣ በጃርሶ ወዘተረፈ መጤ ወራሪ ሠፋሪዎች የተያዘባቸውን ለምና ሰፊ መሬት ለማስመለስ ነው። በመሆኑም አጤ ኢያሱ አድያም ሰገድ በ1696 ዓ.ም ሸዋ

ደብረሊባኖስ መጥተው ከአጤ ልብነ ድንግል ልጅ ያዕቆብ ተወላጅ የሆነውን ነጋሢ ክርስቶስን የሸዋ ገዥ እንዲሆን ሾመውታል። ከእስላሙ የይፋት አርጎባ ወላስማ ባላባት ጋራ ሕብረትን በመፍጠር በወረራ የተያዘባቸውን ለም መሬት እንዲያስመልሱ አጤው አዘዋቸዋል።

በዚህም መሠረት የሸዋ ነጋሢዎች ደረጃ በደረጃ ከነጋሲ ክርስቶስ እስከ ንጉሥ ኃይለ መለኮት የሸዋን አውራጃዎች ከመንዝ ግሼ ሐይቅ ጀምረው በንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ዘመን በደቡብ አዋሽ ወንዝ ማዶ እስከ ጉራጌ አይመለል፤ በምሥራቅ እስከ ጨርጨር ኢቱ ድረስ፤ በምዕራብ ከጎጃም አባይ ወንዝ በመለስ የነበሩትን ባላባቶችን በመስገበር የጥንት ሸዋን አቅንተዋል። ልጃቸው ንጉሥ ኃይለ መለኮት አሩሱን ለማስገብር ዘምተው ሲመለስ በወባ ተንድፈው ታመው እያሉ ነበር የአጤ ቴዎድሮስ ጦር ሸዋን ለመስገበር የመጣው። ኃይለ መለኮት ለውጊያ ሲዘጋጁ ድንገት ስለሞቱ ጠራ ገሊላ ደብረ በግዕ ተቀብረው የሸዋ ጦር ያለ መሪ ተዋግቶ ሲሸነፍ ጥቂቶቹ መኳንንት ልጃቸውን ምንሊክ ይዘው ሳጤ ቴዎድሮስ ገበሩ። አጤ ቴዎድሮስም ያ12 ዓመቱን ልጅ ምኒልክን ወስደው አሳደጉት። በአጤ ቴዎድሮስ ዘመን ሸዋ ሁለት ጊዜ ተወሮ ተምዝብሯል። በቀደሙት ነጋሲዎች ጠንካራ መሪነት ቀንተውና ተባብረው የነበሩት አውራጃዎች ሁሉ ተመልሰው በየባላብቶች እጅ ወድቀው ነበር። የኃይለ መለኮት ታናሽ ወንድም አቤቶ ስይፉ ሣህለ ስላሴ የቴዎድሮስን ወኪሎች ከአንኮበር አባሮ የሸዋን ነፃነት ሲያስመልስ ሲነሳ የቴዎድሮስ ጦር ዳግም ዘምቶ የሸዋን መኳንንት እጅና እግር ቆርጠው፣ የአንኮበር ከተማ አድባራቱን ቅርስና ንብረት እንኳ ሳይቀር ዘርፈው ተመልሰዋል። አቤቶ ሰይፉ ግን በአንኮበር ሙቅምድር ላይ በከፍተኛ ጅግንነት ተዋግቶ ሲሸነፍ ወደ አዳል አርጎባ ወገኖቹ ዘንድ በመሄድ ተርፏል።

በሸዋ ከቴዎድሮስ ዘመን እስከ ምኒልክ ከመቅድላ ግዞት አምልጦ መንገሥ ድረስ የሰሜን ኢትዮጵያ ዓይነት ሥር የሰደደደ መጥፎ በሽታ፣ ማለትም በአውራጃዎቹ ውስጥ አምባገነን ባላባቶችና ሽፍቶች ዘወትር በባላገሩ ሕዝብ ላይ የሚያደርጉት ዝርፊያ፣ ሕገወጥ ድርጊት፣ የነበረው ማኅበራዊ ቀውስና ሕግና ሥርዓትየለሽነት በጣም ተስፋፍቶ ነበር።

ምኒልክ የሸዋ ንጉሥ ከሆኑ ጀምሮ ዋና ሠፈራቸውን ልቼ ደብረብርሃን አጠገብ አድርገው ያያታቸውን የንጉሥ ሣህለ ስላሴን ዕቅድና ዝግጅት ማለትም በግራኝ ጊዜ ተነጥሎ የቀረውን ያማራውን አገር ሁሉ መልሶ ለማዋሃድ በየዓመቱ ዘመቻ ያደረጉ እንድነበረው ተግባራዊ ለማድረግ ቆርጠው ተነሱ።

የሸዋው ታላቅ ንጉሥ ሣህለ ስላሴ አገር የሚለማው ልዩ ልዩ መሣሪያዎችን በመዘጋጀት መሆኑን የተረዱት የእደ ጠበብ ባለሙያ ግንበኞችን፣ አናጢዎችን፣ ሸማኔዎችን፣ ባለጆችን፣ ሸክላ ሠሪዎችን፣ ቆዳ ፋቂዎችን፣ ዣን ሸላሚዎችን፣ የጠመንጃ ባሩድና አረር ሠራተኞችን ሁሉ በማበረታታ፣ ደስ በማሰኘት፣ ልዩ ሽልማትና ድርጎ በመስጠት የታወቁ ናቸው።

ንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ከአውሮፓ ታላላቅ መንግሥታት ማለትም ከታላቋ ብሪታኒያ (በ1834 ዓ.ም) እና ከፈረንሳይ (በ1836 ዓ.ም) ጋራ የንግድ ውል ስምምነት አድርገዋል። የእንግሊዙ መልክተኛ የነበረው ሻምብል ሃሪስ በሸዋ አንጎለላ ከተማ የወዳጅነትና የንግድ ስምምነቱ ለመፈራረም ቆይቶ ሲመልስ የጻፈው መጽሓፍ (W. Harris: Highlands of Ethiopia: London , 1844) የሸዋን መንግሥትና ሕዝብ ታሪክ በሰፊው ያስረዳል።

በሸዋ ሀገር የሰሜን ኢትዮጵያ የዘመነ መሳፍንት አምባገነኖች የርሰ በርስ ሹኩቻ፣ ትርምስ፣ እልቂትና ግድያ ሳይኖር ሕግና ሥርዓት ተከብሮ፣ እስላምና ክርስቲያኑ ተባብሮ፣ ሰላምና እርጋታ ሰፍኖ ቢኮኖሚና ፖለቲካ ጠንካራ መንግሥት ለመምሥረት ተችሏል።

ስለዚህም ነው ዳግማዊ አጤ ምኒልክ የጥንት ኢትዮጵያ ክፍለ ሀገራት የነበሩትን በደቡብና ምሥራቅ መልሶ ለማዋሃድ፣ የኢምፔሪያሊስቶችን ከበባና ወረራ ድል አድርገው ኢትዮጵያ የዓለም ጥቁር ዘርያዎችና ጭቁን ሕዝቦች ሁሉ የነፃነት መሪ ኮከብ እንድትሆን ያበቁዋት።

ከሰማያዊ ፓርቲ አቶ የሸዋስ የርሻ መሬትና የከተማ ቦታ በግል ይዞታ ሥር መያዝ አለበት ከማለት በስተቀር በአዲስ አበባ ሕዝብ ላይ ስለሚሸረበው ሴራና ኢኮኖሚያዊ ምዝበራ፣ የሰብእአዊ መብት ጥሰት አስመልክቶ ያሰሙት ተቃውም በጣም አነስተኛ ነው። ሐቀኛው ጠበቃ ተማም አባቡልጉ በዝርዝር ሲያስረዱን ለምን ተቃሚ ተብዬዎቹ ፈራ ተባ ይላሉ!!

በዚህ ዓይነት ታማኝ ተቃዊሚዎች በአዲስ አበባ ረጺ ቆሼ ሰፈር በጣም ብዙ ሰው ሲያልቅና ሲፈናቀል እንኳ ምንም ማድረግ የማይችሉት የወያኔ ትግሬ አጃቢዎችና አዳማቂዎችን ማየትና መስማት በጭራሽ አንፈልግም። ስላማዊ ትግል እያላችሁ መሞዳሞዳችሁን አቁሙ።

ቆራጥ የኢትዮጵያ ልጆችን በይስሙላ ተቃዋሚነት ጨንበል በወያኔ እየታደኑ እንዲያልቁ፣ እንዲታሰሩ፣ እንዲሰደዱ የሚደረገው ሴራ መቆም አለበት።

የአዲስ አበባ ከተማ ነፃ ትወጣላች!     የሸዋ ግዛትና መንግሥት ዳግም ይነሳል!
የሸዋ አበባ ያብባል ገና!
የወያኔ ትግሬ ባንቱስታን የጎሣ ክልል እስር ቤት ይፈርሳል!

የሸዋ ሕዝብ ድርጅት Shoa People Organisation (SPO)     www.shoa.org

አፈ ጉባ፥ ቢትወደድ ኃይለ ልዑል ማንበግሮ ግዛቸው

አባሪ፣ የሀገረ ሸዋ አዲስ አበባ ካርታን ይመልከቱ

fig. 2 : Shoa and its *awrajja* before 1987

